# ለኢትዮጵያውያን ዳያስፖራዎች የተዘጋጀ የቤት መሥሪያ ወይም መግዣ ብድር

የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በውጭ ለሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እና ትውልደ ኢትዮጵያውያን የቤት መሥሪያ ወይም መግዣ የብድር አገልግሎት አቅርቧል።

## በዚህ አገልግሎት እንዴት ተጠቃሚ መሆን ይቻላል?

- ማንኛውም ዕድሜው 18 ዓመትና ከዚያ በላይ የሆነ ዳያስፖራ የብድር ጥያቄ ማቅረብ የሚችል ሲሆን፣ በሚያቀርብበት ጊዜም የሚከተሉትን ሰነዶች ማሟላት ይኖርበታል፤
    - ✓ የመኖሪያ እና/ወይም የሥራ ፈቃድ፣
    - ✓ አመልካቹ ኢትዮጵያዊ ከሆነ የታደሰ ፓስፖርት ወይም ትውልደ ኢትዮጵያዊ የሆነ የውጭ ዜጋ ከሆነ የታደሰ መታወቂያና የትውልደ ኢትዮጵያውያን መታወቂያ (ብጫ ካርድ)፣
    - ✓ ሁለት የቅርብ ጊዜ የፓስፖርት መጠን ያለው ፎቶግራፍ፣
    - ✓ የጋብቻ የምስክር ወረቀት፣ ወይም ያላገባ ከሆነ ይህንኑ የሚያረጋግጥ ሠነድ፣
    - ✓ ብድሩ የተጠየቀው በወኪል አማካይነት ከሆነ የወኪሉ የታደሰ መታወቂያ ኮፒ እና ሁለት ፓስፖርት መጠን ያለው የቅርብ ጊዜ ፎቶግራፍ እና የውክልና ማስረጃ፣
    - ✓ እንደአስፈላጊነቱ ጠቅላላ ዓመታዊ የደመወዝ መጠን እና የተጣራ ገቢን የሚገልጽ ከቀጣሪው የተሰጠ የቅጥር ደብዳቤ፣
    - ✓ እንደአግባብነቱ የቅጥር ውል ኮፒ፣
    - ✓ ከውጪ ሀገር ባንክ ቢያንስ የአንድ ዓመት የሂሳብ መግለጫ
    - ✓ አመልካቹ በንግድ ሥራ የሚተዳደር ከሆነ፤
        - ቢያንስ የሦስት ተከታታይ ዓመታት የሂሳብ ዝርዝር መግለጫ፣
        - የታደሰ የንግድ ፈቃድ እና የንግድ ምዝገባ የምስክር ወረቀት፣ እና
        - የግብር ክፍያ ምስክር ወረቀት ማቅረብ ይኖርበታል።
- አመልካቹ የመኖሪያ ቤት መሥሪያውን ወይም መግዣውን ቢያንስ 20 በመቶ በውጭ ምንዛሪ ማስገባት አለበት።
- ባንኩ የሚሠራውን ወይም የሚገዛውን ቤት እስከ 80 በመቶ ወጪ ያበድራል።
- ብድሩ በባንኩ ተቀባይነት ባላቸው የውጭ ገንዘቦች (የአሜሪካን ዶላር፣ የእንግሊዝ ፓውንድ ወይም በዩሮ) መከፈል አለበት።

## የቤት መሥሪያ ወይም መግዣ የቁጠባ ሂሳብ የት መክፈት ይቻላል?

- አመልካቹ በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቅርንጫፎች ወይም በሚኖርበት ሀገር በሚገኝ የኢትዮጵያ ኤምባሲ በአካል በመቅረብ ወይም በሕጋዊ ወኪሉ አማካይነት የቁጠባ ሂሳብ በመክፈት የብድር መዋጮውን መቆጠብ ይችላል።
- አመልካቹ የሚፈለግበትን መዋጮ እንዳሟላ የብድር ጥያቄውን ለማንኛውም የባንኩ የኮንስዩመርና የቤቶች ብድር ማዕከላት ወይም ከአዲስ አበባ ውጪ ባሉ የዲስትሪክት ቢሮዎች ማቅረብ ይችላል።

## የቤት መሥሪያ/መግዣ ብድር ባህሪያት

- የብድር አገልግሎቱ ለመኖሪያ ቤት መሥሪያ/መግዣ የሚውል ነው።
- የብድሩ መክፈያ ጊዜ ከ20 ዓመት ሊበልጥ አይችልም።
- የብድር መዋጮው የሚሠራውን ወይም የሚገዛውን ቤት የመሀንዲስ ግምት ቢያንስ 20 በመቶ ይሆናል።
- የወለድ ምጣኔ ቢያንስ በዓመት 8.5 በመቶ ነው።
- ዳያስፖራው ያለበትን ቀሪ እዳ ያለተጨማሪ ክፍያ በፈለገበት ጊዜ አጠናቆ መክፈል ይችላል።

**አድራሻ** : ጋምቢያ ጎዳና
**ስልክ** : +251-11-551-95-06 +251-11-551-50-04 **ፖ.ሣ.ቁ** : 255 አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ
**ፋክስ** : +251-11-554-62-43
**የስዊፍት አድራሻ** : CBETETAA
**ድረ ገፅ** : www.combanketh.et
**ኢ.ሜይል** : cbecomu@combanketh.et
www.facebook.com/combanketh
www.twitter.com/CBE
www.youtube.com/Commercialbankofethiopia